# የበቆጂ ጨፋ መካነ ሕይወት መድኃኔ ዓለም ደብረ ቁስቋም አንድነት ገዳም መገደም መነሻ ትርክቶች

ፍሬ ሕይወት ባዩ*


## Abstract

Monastery (gädam in Amharic) is among the most important institutions of the EOTC. According to the church’s tradition, monasteries and monasticism came to existence with the arrival of the Nine Saints. Ethiopian monasticism becomes more organized and revived in the 13th century through the activities of some well-known monastic figures such as St.Teklehaimanot. This monastic life is either coenobitic (andennat) which stresses communal life style or idiorythemic that allows monks to have private possessions. The objective of the current study is to analyze the kind and nature of narratives which are believed to be created by the founder of Mäkanä Hiwot Mädhane 'Aläm Däbrä Qusqʷam coenobitic monastery, Ǝmmahoy Sahlä Mariyam. The data were collected through open-ended interviews and participatory observations. As the study shows, these narratives are responsible for the establishment of the monastery in 1994 along with two churches. Moreover, more than 42 holy water sites were blessed by the local priests and begun to serve the local community. This new monastery, in which more than 32 monks live, was first established in 2010 as women’s andïnnät gädam. Later in 2011, it became men’s and women’s andïnnät  gädam


*ፍሬ ሕይወት ባዩ በፎክሎር የሦስተኛ ዲግሪ ያላቸው ሲኾኑ በአዲስ አበበባ ዩንቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች አካዳሚ፣ የፎክሎር ተመራማሪ ናቸው።

## ፩. መግቢያ

የጥናት ወረቀቱ ሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ያሉት ሲኾን፣ የመጀመሪያው ክፍል ስለ ጥናቱ አጠቃላይ ገለጻ የተደረገበትን መግቢያ የያዘ ሲኾን፣ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ በርእሰ ጉዳዩ ላይ ቀደም ብለው የተሠሩ የንድፈ ሐሳብና የተዛማጅ ጥናቶች ውጤቶች ምጥን በኾነ ስልት የተዳሰሱበት ክፍል ነው፡፡ ሦስተኛው ክፍል የጥናቱ ዋና አካል የኾነው የበቆጂ ጨፋ መካነ ሕይወት መድኃኔ ዓለም ደብረ ቁስቋም አንድነት ገዳምን በመገደም ሂደት ዙሪያ የሚነገሩ ትርክቶች[1] የተተነተኑበት ሲኾን፣ የመጨረሻው ክፍል ማጠቃለያ እና የዋቢ ጽሑፎች ዝርዝርን ይዟል፡፡

የዚህ ጥናት ትኩረት የኾነው የአንድነት ገዳም በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት በአርሲ ዞን ሌሙና ቢልቢሎ ወረዳ ከዞኑ ዋና ከተማ ከአሰላ በዐምሳ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ፤በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በአርሲ ሀገረ ስብከት ይገኛል፡፡ ገዳሙ ከአዲስ አበባ ፪፻፴ ኪሎ ሜትር ገደማ ይርቃል፡፡ ጥናቱ ትኩረት የሚያደርገው በሀገረ ስብከቱ ውስጥ ከሚገኙ ገዳማት መካከል በ፳፻፫ ዓ.ም. በተመሠረተው “የአንድነት ገዳም” ላይ ይኾናል፡፡ የጥናቱ አነሣሽ ምክንያት ከዚህ በፊት በገዳሙ በተለይም በጠበሉ[2] ላይ ጥናት ሳደርግ መረጃዎቹን ከሰጡኝ ሰዎች መካከል የነበሩት፤ በተለይም ለገዳሙ መልሶ መገደም ምክንያት ከነበሩት እና ዛሬ በአካለ ሥጋ ከዚህ ዓለም ከተለዩት እናት ያገኘሁት ቀዳሚ መረጃ ስላስገረመኝ በዚህ የጥናት ቅርጽ መዝግቦ ለማቆየት ከመነጨ ፍላጎት ነው፡፡

ይህ በዚህ ጥናት የሚቀርብ መረጃ ወደ ፊት ስለ ገዳሙም ኾነ ስለ መሠረቱት እናት ታሪክ ሲጻፍ “በቃል ያለ ይረሳል በጽሑፍ ያለ ይወረሳል” እንደሚባለው መታተሙ ጠቃሚ ይኾናል በሚል ዕሳቤ ነው፡፡ በተለይም ጽሑፉን ለኅትመት የሚያበቃው መጽሔት ተደራሽነቱ በመሰል ርእሰ ጉዳይ ላይ ለሚሠሩ አጥኚዎች ቅርብ በመኾኑ ፍላጎት ላለው አጥኚ መረጃ የመስጠት ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በተለይም በዚህ ጥናት የሚቀርቡ ትርክቶች እንደሚጠቁሙት አሁን መልሶ የአንድነት ገዳም የኾነው ይህ ገዳም ቀደም ሲል “በግራኝ አህመድ[3] የወደመ ገዳም ነበረ” የሚለው ሰፊ የታሪክ፣ የአርኪዎሎጂ እና

[1] “ትርክት” የሚለው ቃል በዚህ ጽሑፍ አገባብ ስለ ገዳሙ አመሠራረት በቃል የሚነገሩ አፈ-ታሪኮችን፣ ትውፊቶችን እንዲሁም ምስክርነት የተሰጠባቸው ሃይማኖታዊ ነገራዎችን የሚመለከት ነው፡፡

[2] ወርቁ ከተማ በ፲፱፻፺፱ዓ.ም. ስለዚህ ገዳም ጥናት አድርጓል፡፡ የጥናቱ ዓላማ የገዳሙን አመሠራረት፣ በገዳሙ ሥር ስለሚገኘው ጸበል እና የማጥመቅ ሥርዓት እንዲሁም የመነኮሳቱን ድርጊቶች ፎክሎራዊ ገጽታ ማሳየት እንደ ኾነ አስፍሯል፡፡ የገዳሙን መመሥረት ተከትሎ የሚነገሩ ሥነ ቃሎች እና ትረካዎች ፎክሎራዊ ገጽታ ምን እንደሚመስል አሳይቷል፡፡ የወርቁ ጥናት የገዳሙን አመሠራረት መግለጹ ከዚህ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል፡፡ ኾኖም የዚህ ጥናት ትኩረት የገዳምን ፅንሰ ሐሳብ በመያዝ ለገዳሙ መመሥረት ምክንያት በኾኑ ትርክቶች ላይ ብቻ በማተኮር ከፎክሎራዊ ይዘት ይልቅ ሃይማኖታዊ ይዘቱን ተከትሎ የቀረበ በመኾኑ ከወርቁ ጥናት የተለየ ያደርገዋል፡፡

[3] በተለምዶው ግራኝ አህመድ ተብሎ የሚታወቀው የጦር መሪ ሙሉ ስሙ ኢማም አህመድ ኢብን ኢብራሂም አልጋዚ ሲኾን የኖረውም ከ ፲፭፻፯ እስከ ታኅሣሥ ፳፩፣ ፲፭፻፵፫ እ.ኤ.አ ነበር፡፡

የመሰል የሙያ መስኮችን ጥናት የሚፈልግ በመኾኑ ሌሎች አጥኚዎች ከትርክቶቹ በመነሣት በቦታው ላይ ጥናት እንዲያደርጉ ያነሣሣል፡፡

**በጥናቱ የተመለሱ የምርምር ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡**

፩. የጨፋ መካነ ሕይወት መድኃኔ ዓለም ደብረ ቁስቋም አንድነት ገዳም እንዲመሠረት ምክንያት የኾነውን ትርክት ማን ተናገረው?

፪. የጨፋ መካነ ሕይወት መድኃኔ ዓለም ደብረ ቁስቋም አንድነት ገዳም እንዲመሠረት ምክንያት የኾኑ ትርክቶች ይዘት ምን ነበረ?

፫. የጨፋ መካነ ሕይወት መድኃኔ ዓለም ደብረ ቁስቋም አንድነት ገዳም ስለ ተገደመበት ቦታ ዳራ ትርክቶቹ ምን ይላሉ?

፬. ከትርክቶቹ ወደ ተግባር የተቀየሩት የትኞቹ ናቸው?

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ለበቆጂ ጨፋ መካነ ሕይወት መድኃኔ ዓለም ደብረ ቁስቋም አንድነት ገዳም መገደም መነሻ የኾኑ ትርክቶችን መተንተን ሲኾን፣ ዝርዝር ዓላማዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

፩. የበቆጂ ጨፋ መካነ ሕይወት መድኃኔ ዓለም ደብረ ቁስቋም አንድነት ገዳም እንዲገደም መነሻ የኾኑ ትርክቶችን ባለቤት (ተናጋሪ) ማንነት ማስተዋወቅ፣

፪. የበቆጂ ጨፋ መካነ ሕይወት መድኃኔ ዓለም ደብረ ቁስቋም አንድነት ገዳም እንዲገደም ምክንያት የኾኑ ትርክቶችን ይዘት ማብራራት፣

፫. የበቆጂ ጨፋ መካነ ሕይወት መድኃኔ ዓለም ደብረ ቁስቋም አንድነት ገዳም የተገደመበትን ቦታ ዳራ አስመልክቶ የተነገሩ ትርክቶችን ለይቶ መግለጽ እንዲሁም፣

፬. የትርክቶቹን ይዘት ተከትሎ በተግባር የተሠሩትን ትርክቶች መዘርዘር የሚሉ ናቸው፡፡

ጥናቱ መሠረት ያደረገው መረጃ፣ ቀዳማይ የመረጃ ምንጭን ነው፡፡ ቀዳማይ የመረጃ ምንጩ ከመስክ የተገኘ መረጃ ነው፡፡ በመስክ ምርምር ለሚጠየቁ ጥያቄዎች ምላሽ ለማግኘት ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅ፣ የቡድን ውይይት እና የጽሑፍ መጠይቅ አገልግሎት ይሰጣሉ (ኮተሪ ፳፻፬፣ ገጽ ፺፮)፡፡ ለዚህ ጥናት ቃለ መጠይቅ እና ምልከታ ዋንኞቹ የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች ኾነው አገልግለዋል፡፡ በዚህ ጥናት ዋና የመረጃ ምንጭ ከኾኑት ግለሰብ በቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ በገዳሙ ውስጥ በአካል በመገኘትና ምልከታ በማድረግ የበለጠ ዳብሯል፡፡

ይህ ጥናት የምልከታ ዘዴን መጠቀሙ ትርክቶቹ ምን ያህል ተግባር ላይ ዋሉ? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ አስችሏል። እንዲሁም በምልከታ የተሰበሰቡ መረጃዎች ግልጽ ያልኾኑ ስለ ነበሩ እነዚህም በቃለ መጠይቅ ምላሽ አግኝተዋል። ቃለ መጠይቅ በዋናነት ለገዳሙ መገደም መሠረት የኾኑትን ትርክቶች ለማግኘት አገልግሏል። ለዚህ ጥናት መረጃ አቀባይ የኾኑ ሰዎች የተለያዩ መስፈርቶችን በመጠቀም ተመርጠዋል። በመጀመሪያ ለገዳሙ መልሶ መገደም መሠረት የኾኑት እናት በቃለ መጠይቅ ዘዴ መረጃ በመስጠት ሰፊውን ቦታ ሸፍነዋል። ከገዳሙ ምሥረታ በፊት በአካባቢው ይኖሩ የነበሩ ነዋሪዎች እንዲሁም በገዳሙ ከሚኖሩ መነኰሳት መካከል በዓላማ ንሞና ተመርጠው መረጃዎች ተሰብስበዋል። በመጨረሻም በተለያዩ አጋጣሚዎች ለተወሰኑ ለገዳሙ ቅርበት ላላቸው ግለሰቦች ጥያቄዎችን በማቅረብ የሰጧቸውን ምላሾች ቀድሞ ከተገኘው መረጃ ጋር ለማመሳከር ተሞክሯል።

የመረጃ አተናተን ዘዴ፤ ከላይ በተጠቀሱት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች አማካኝነት የተሰበሰቡ መረጃዎችን ለመተንተን ገላጭ የምርምር ስልት ተመርጧል። ይህ ዘዴ መመረጡ የገዳሙን ቀዳማዊ ዳራ እና አሁን የአንድነት ገዳም ኾኖ ከተደራጀ በኋላ ያለውን የገዳሙን ኹኔታ ለመግለጽ እንዲረዳ ነው።

## ፪. የፅንሰ ሓሳብ ዳራ፤ ገዳም፣ ገዳማዊነት እና ምንኵስና

የእስክንድርያው ፓትርያርክ ቅዱስ አትናቴዎስ በጻፉት የእንጦንስ የሕይወት ታሪክ መሠረት የመጀመሪያው ምንኵስና መሥራች አባት ቅዱስ እንጦንስ (፪፻፶፩-፫፻፶፮ ዓ.ም.) ነው። ምንም እንኳን የብህትውና ኑሮ የተመሠረተው በአባ እንጦንስ ቢኾንም ትንሽ ቀደም ብሎ በንጉስ ዳክዮስ ትእዛዝ በክርስቲያኖች ላይ በታወጀው ስደት ምክንያት ግብጻዊው መናኝ አባ ጳውሊና (ጳውሎስና) መሰሎቹ ዓለም በቃን በማለት በየጊዜው ወደ ግብጽ በረሓዎች እየተሰደዱ ከሰው ሳይገናኙ በተለያዩ ዋሻዎች ይኖሩ እንደ ነበር ገልጸዋል (ጂ.ርፓኒልስ፣ ፲፱፻፺፩፣ ገጽ ፻፶፫፤ ያረጋል፣ ፲፱፻፺፫፣ ገጽ ፻፹፭፤ ሉሌ፣ ፲፱፻፹፮፣ ገጽ ፹፯)።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የምንኵስና ታሪክ አባ እንጦንስ ምንኵስናን የተቀበለው በቅዱስ ሚካኤል እጅ እንደ ኾነ ይታመናል። የመጀመሪያውን ገዳማዊ ሕይወት የወጠነው እርሱ ነው። በኋላም ከዚያ ወጥቶ ከቀይ ባህር ፴ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በደብረ ቁልዝም በኣት አጽንቶ መኖር ጀመረ። በሕይወቱ መጨረሻ "የባህታውያን አባት ከሚባለው ከአባ ጳውሊ ጋር ተገናኝቶ ነበር (ዳንኤል፣ ፳፻፲፩፣ ገጽ ፯፻፲፪-፯፻፲፫)።" የገዳም መመሥረት ዋና ዋና ምክንያቶች ከዘመነ ኔሮ እስከ ታላቁ ቆስጠንጢኖስ (ከ፫፻፮-፫፻፴፯ ዓ.ም.) ድረስ በክርስቲያኖች ላይ የመጣው ስደት፣ አማኞች

በጠንካራ የወንጌል ስርጭታቸው እንዲሁም ለባህላዊ አምልኮ ላለመታዘዝ በወሰዱት አቋም እና ወንጌል ሰዎችን ወደ ገዳም ይገቡ ዘንድ አመላክቷል የሚለው አመለካከት እንደ ኾነ ጽፈዋል (ስሜ፣ ፳፻፲፩፣ ገጽ ፻፴፫)፡፡

የገዳም ሕይወት የክርስትና ሃይማኖት ከመጀመሩ በፊት በምሥራቅ እና በሩቅ ምሥራቅ ባሉ አገራት ውስጥ በሚገኙ ሃይማኖቶች እንደ ተጀመረ የሚገልጹ መረጃዎችም አሉ። ከሃይማኖቶቹ መካከል ዋና ዋናዎቹ ቡድሂዝም፣ ሂንዱይዝም፣ ብራህማኒዝም እና የአይሁድ እምነት ይጠቀሳሉ (ምክረ ሥላሴ፣ ፳፻፣ ገጽ ፫፻፶፰)፡፡ በአይሁድ እምነት የምነና እና የምንኩስና ሕይወት የተለመደ ነው፡፡ በዚህም ናዝራውያን በሚል መጠሪያ ከማኅበረሰቡ ተለይተው በብቸኝነት የሚኖሩ ሰዎች እንደ ነበሩ ይገልጻሉ (ዝኒ ከማሁ)።በኢትዮጵያ ገዳማዊ ሕይወት የተጀመረው በ፭ኛ መ.ክ.ዘ. አካባቢ ሲኾን የተጀመረው ከዘጠኙ ቅዱሳን ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ጋር ተያይዞ ነው፡፡ በተለይ ከዘጠኙ ቅዱሳን አንዱ የኾኑት አባ ዐረጋዊ (ዘሚካኤል) የአባ ጳኩሚስ ተከታይ የነበሩት የአባ ቴዎድሮስ ደቀ መዝሙር ስለ ነበሩ በገዳመ አስቄጥስ የተመሠረተውን ሥርዓተ ምንኩስና ጠንቅቀው ያውቁ ነበር፡፡ ስለዚህ ከጓደኞቻቸው ጋር በመኾን የምንኩስናን ሥርዓት ደብረ ዳሞ ገዳም አቋቋሙ (ሰለሞን፣ ፳፻፩፣ ገጽ ፻፲፮፤ ሉሌ፣ ፲፱፻፹፮፣ ገጽ ፻፳፩-፻፳፮)፡፡

ስለ ገዳም ምንነት በርከት ያሉ ሰዎች ጽፈዋል፡፡ ከእነዚህ ምሁራን መካከል ኪዳነ ወልድ ክፍሌ አንዱ ናቸው፡፡ እንደ እርሳቸው ፍቺ ገዳም ማለት “ገዳም (ማት፣ እብ፣ ሚቅላጥ) በቁሙ ምኔት፣ ደብር፣ የመነኮሳት ሰፈር፣ ታላቅ ቤተ ክርስቲያን፣ በደለኛ ሸሽቶ የሚጠጋበት፣ ደውሎ የሚማጠንበት ደብር፣ ምስካይ፣ ዱር፣ ጫካ፣ ወማ፣ በረሀ፣ በዳ፣ ከሀገር ከመንደር የራቀ የአራዊት ክፍል…” ማለት ነው (ኪዳነ ወልድ፣ ፲፱፻፵፰፣ ገጽ ፫፻፪)፡፡ እንዲሁም የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች አካዳሚ ባዘጋጀው የአማርኛ መዝገበ ቃላት “ገዳም መነኮሳት ከዓለማዊ ኑሮ ተገልለው በሃይማኖታዊ ሥርዓት እና ደንብ እየተዳደሩ የሚኖሩበት ቤተ ክርስቲያን ሲኾን አንድ ሰው ገዳም ገባ ሲባል ዓለማዊ ኑሮን በመተው መንፈሳዊ ኑሮን ለመኖር መቀመጥ ጀመረ ማለት ነው” (፳፻፮፣ ገጽ ፭፻፮)፡፡

በዚህ ክፍል የሚነሣው ሌላው ጉዳይ “ምንኩስና” ነው፡፡ ምንኩስና የሚለው ቃል “monahos” ከሚለው የግሪክ[4] ቃል የመጣ ሲኾን ትርጉሙም ብቸኛ ማለት ነው፡፡ ‘መንኮሰ’፤ ሞተ ማለት ነው:: ሞተ ሲባል ከዚህ ዓለም ተለየ፤ ዓለምን ናቀ ተወ ማለት ነው፡፡ ብህትውና የሚለው ቃል ደግሞ ተባሕተወ ከሚለው የግእዝ ግስ የወጣ ሲኾን ትርጉሙም ብቸኛ ኾነ ተለየ ተነጠለ ማለት ነው (ምክረ ሥላሴ፣ ፳፻፣ ገጽ ፫፻፶፰)፡፡ ብቸኛ ኾነ

[4] በግሪክ ቋንቋ “καλόγερος”

ማለት ከዓለምም ከመነኮሳትም እንኳ ተለይቶ መኖርን ያሳያል፡፡ መነኩሴም ኾነ ባህታዊ የሚለው ትርጉማቸው ከሌላው የማኅበረሰብ ክፍል ተለይተው ለብቻ የሚኖሩ እንደ ኾኑ ይጠቁማል፡፡ ምንኩስና ራሳቸውን ለፈጣሪ ለማስገዛት እና ለፈጣሪ ለማቅረብ፣ ይህንን ዓለም ንቀው ሀብት ንብረታቸውን ትተው፣ ከዘመድ አዝማድ ተለይተው አምላካቸውን ለማገልገል በዋሻ፣ በዱር፣ በበረሀ አራዊትን ሳይፈሩ በገዳም ተወስነው የሚኖሩበት ሕይወት ነው፡፡ መነኮሳቱ ወይም ባህታውያኑ የብቸኝነትን ሕይወት የሚመርጡበት ምክንያት የሚኖሩበትን ዓለም በመናቃቸው ምክንያት እንደ ኾነ ሊቃውንት ያስረዳሉ (ምክረ ሥላሴ፣ ፳፻፣ ገጽ ፫፻፶፱-፫፻፷፩)፡፡

የገዳም ኑሮ ዓይነቱ ይለያያል፡፡ በእኛ ሀገር በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በግል የሚደረግ የገዳም ኑሮ ዓይነቱ “ቁሪት” ይባላል፡፡ በሁለተኛነት የሚጠቀሰው የገዳም ሕይወት በርካታ ሰዎች በአንድነት የሚኖሩበት ሥርዓት ነው፡፡ ይህንን ሥርዓት በማስጀመር አባ ጳኲሚስ ይጠቀሳሉ፡፡ አባ ጳኲሚስ በ፫፻፳፫ ዓ.ም. አንድ መልአክ በራእይ ተገልጾላቸው በላዕላይ ግብጽ በዐባይ ባሕር አጠገብ “ታቤኒ” በሚባል ስፍራ አንድ የመነኮሳት መኖሪያ መመሥረታቸው እና የገዳሙን ሕግ ማውጣታቸው ይነገራል (ምክረ ሥላሴ፣ ፳፻፣ ገጽ ፫፻፷፱-፫፻፸፤ ገሰሰ፣ ፲፱፻፺፰፣ ገጽ ፲፩-፲፫)፡፡ የዚህ ዓይነቱ የገዳም አስተዳደር በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን “የአንድነት” ገዳም ይባላል፡፡ በአንድነት ገዳም ገዳማውያኑ በማኅበር እንደየ ችሎታቸው እና እንደየ ፍላጎታቸው በተለያዩ አገልግሎቶች ላይ ይሳተፋሉ፡፡ ገዳማውያኑ ሙሉ በሙሉ ለገዳሙ ሕግ ተገዢ ሲኾኑ በገዳሙ የተቀመጠውን የአለባበስ፣ የአመጋገብ፣ የአሠራር ሕግ እና ደንብ እንዲያከብሩ ይገደዳሉ (ሞገስ፣ ፳፻፫፣ ገጽ ፴፯)፡፡

## ፫. ለበቆጂ ጨፋ መካነ ሕይወት መድኃኔ ዓለም ደብረ ቁስቋም አንድነት ገዳም መገደም መነሻ ትርክቶች

የበቆጂ ጨፋ መካነ ሕይወት መድኃኔ ዓለም ደብረ ቁስቋም አንድነት ገዳም በአርሲ ዞን ሌሙና ቢልቢሎ ወረዳ በጨፋ ቀበሌ ገበሬ ማኅበር ይገኛል፡፡ ከ፲፱፻፸ዎቹ ዓ.ም. በፊት ጀምሮ በተለምዶ “የአስታጥቄ ምንጭ” በመባል የሚታወቅ የአካባቢው ነዋሪዎች ለመጠጥ ውሃ ሲገለገሉበት የነበረ ምንጭ ያለበት ቦታ ነበር፡፡ ጠዋት ጠዋት ከምንጩ በሚቀዳ ውሃ በመታጠብ እንደ ችፌ፣ እከክና ልዩ ልዩ የቆዳ በሽታ ያለባቸው ሰዎች በተወሰነ ደረጃ ከበሽታቸው ይፈወሱም ነበር (ፍሬ ሕይወት፣ ፳፻፲፮ እ.ኤ.አ)፡፡ በምንጩ ውሃ ይጠቀሙ ከነበሩ የመንደሩ ነዋሪዎች መካከል እመት የሺሐረግ ይገኙበታል፡፡ እመት የሺሐረግ ዓለሙ ትውልዳቸው በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በቀድሞ አጠራሩ ጎንደር ግዛት ጋይንት ወረዳ ልዩ ስሙ ጨጨሆ መድኃኔ ዓለም ሲኾን ወደ አርሲ ዞን የመጡት በ፲፱፻፸፯ ዓ.ም. ነበር፡፡

ዛሬ "ጨፋ መካነ ሕይወት መድኃኔ ዓለም ደብረ ቁስቋም አንድነት ገዳም" እንዲመሠረት ምክንያት የኾኑት እናት የተናገሯቸውን ትርክቶችና ሌሎችም እንደ አስፈላጊነቱ አይተናል ያሉት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ ቀደም ሲል እመት የሺ ሐረግ በኋላ እማሆይ ሳህለ ማርያም ይባሉ ነበር፡፡

## ፫.፩. ለገዳሙ መገደም መነሻ የኾኑ ትርክቶችን ተራኪ ማንነት

እመት የሺሐረግ በቀድሞ አጠራር ጎንደር ግዛት ጋይንት በሚባለው ልዩ ስፍራ ከአባታቸው ከአቶ ዓለሙ ወርቅነህና ከእናታቸው ከወ/ሮ ፀሐይነሽ ዳርጌ በ፲፱፻፵፫ ዓ.ም. ተወለዱ፡፡ እመት የሺሐረግ ነፍስ ካወቁበት ጊዜ ጀምሮ ፀሎታቸው የነበረው "እንደ እንጦስና መቃርስ አስኬማ ደፍቼ ልኑር፤ ይህ ካልኾነ እና በዓለም ኑሪ ካልከኝ እንደ አባቶች እግዚአብሔርን የሚፈራ ከክፋት የራቀ የኑሮ አጋር ስጠኝ፤ የማሕፀኔንም ፍሬ ባርክልኝ[5]" የሚል ነበር፡፡

እመት የሺሐረግ የትዳርን ሕይወት በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን በመፈጸም ዐምስት ወንዶች እና አንዲት ሴት ልጅ አፍርተዋል፡፡ የመጀመሪያ ልጃቸውን ከወለዱ በኋላ የፈጣሪ ትዕዛዝ በተደጋጋሚ በህልም ይደርሳቸው ነበር፡፡ ኾኖም መልእክቱን ለመናገር አልደፈሩም፡፡ መልእክቱን ባለማድረሳቸው በተለያዩ ቅጣቶች ይገሰጹ ነበር፡፡ ለምሳሌ በአንዲት ጀምበር ያለምንም ሕመም ጥርሳቸው በሙሉ ረግፏል፡፡

ለእመት የሺ ሐረግ በራእይ ከተነገራቸው መልእክት አንዱ፤ ከጎንደር ወደ አርሲ እንደሚሄዱ፤ ከሄዱም በኋላ በእርሳቸው አሳሳቢነት ገዳም እንደሚቋቋምና ጠበል ለሕሙማነ ሥጋ ፈውስ ይኾን ዘንድ እንደሚፈልቅ ነው፡፡ ለዚህም ማስረጃ ይኾናቸው ዘንድ በጎንደር ሳሉ በአካባቢያቸው የፈለቀው ጠበል ምልክት ኾኖአቸው ነበር፡፡

እመት የሺሐረግ ወደ አርሲ ክፍለ ሀገር ሌሙና ቢልቢሎ ወረዳ ጨፋ አካባቢ ቀደም ብለው ይምጡ እንጂ የትዳር አጋራቸውና ልጆቻቸው ዘግየት ብለው ተከትለዋቸው ወዳሉበት መጥተዋል፡፡ እሳቸው በትዳር የመቀጠሉ ፍላጎት ባይኖራቸውም ለተወሰነ ጊዜ በአንድ በኩል ትዳራቸውን አክብረው በሌላ በኩል የፈጣሪን ትዕዛዝ ለመፈጸም እየተጉ ከስድስት ዓመት በላይ ኖረዋል፡፡

[5] እማሆይ ሣህለ ማርያም፣ ዕድሜ ፷፫ (ቃለ-መጠይቅ ሐምሌ ፲፩ ቀን፣ ፳፻፲፩ ዓ.ም.)፡፡

የመጨረሻ ልጃቸውን ወልደው በሁለተኛው ወር በራእይ መልእክት ደረሳቸው። መልእክቱም "ንጽህናሽን ጠብቂ ብቻሽን ሁኚ" የሚል ነበረ። በትዳር እያሉ ይህንን ትዕዛዝ መፈጸም ከባድ ቢኾንም እንደ ታዘዙት ለዘጠኝ ወራት ኑሯቸውን በአንዲት አነስተኛ ጎጆ ውስጥ አደረጉ።[6] ሕፃናት ልጆቻቸውን አቅፈው በጾም፣ በጸሎትና በስግደት ሥጋቸውን አደከሙ። በዚህ መልኩ እየኖሩ በመካከሉ እሳቸው እና የመጨረሻ ሕፃን ልጃቸው በጠና ታመሙ። የእሳቸውንም ኾነ የልጃቸውን በጠና መታመም ያዩት አንድ የአካባቢው ነዋሪ ከራሳቸው ልምድ በመነሣት፤ ከቤታቸው ጀርባ ዝቅ ብሎ ከመኖሪያ ቤታቸው የዐስር ደቂቃ መንገድ ርቀት ላይ የሚገኘው እና ለተለያየ አገልግሎት የሚጠቀሙበት የአስታጥቄ ምንጭ የሚባለው የምንጭ ውሃ ለዚህ ዓይነት ሕመም ፍቱን መድኃኒት መኾኑን እና ማልደው ወደዚያው በመሄድ እንዲጠመቁ መከሯቸው።

እመት የሺሐረግ እሑድ ለሰኞ አጥቢያ አንዲት ልጅ አስከትለው ለተለያዩ አገልግሎቶች ይጠቀሙበት ወደ ነበረው ምንጭ በማለዳ አመሩ። በቦታው ደርሰው ወደ ምንጯ ሊገቡ ሲሉ፣ ከምንጩ ጀርባ ድምፅ ይሰማሉ። እመት የሺሐረግም በፍርሃት ተውጠው በቆሙበት በአርምሞ ሲያዳምጡ "አድነኝና ልናገር ዝናህን፣ አድነኝና ልናገር ዝናህን፣ አድነኝና ልናገር ዝናህን እያልሽ ተጠመቂ" የሚል መልእክት ነበረ። እመት የሺሐረግ ወደ ምንጩ ገብተው ሲጠመቁም ያንኑ ድምፅ ሰሙ፣ ድምፁን ሲሰሙ ከምንጩ ወጡ። ድምፁን ለመስማት ሦስት ጊዜ ወጥተው እየተመለሱ ተጠምቀው በሥመ ሥላሴ አማትበው የሚሰማቸው ሰው አጠገባቸው ባይኖርም "ከዳንኩ ለምን አልናገር እናገራለሁ እንጂ" በማለት ምላሽ በመስጠት ወደ ቤታቸው ተመለሱ። በተደጋጋሚ ለዐምስት ቀናት በምንጩ ውሃ ተጠምቀው ሙሉ በሙሉ ከህመማቸው ዳኑ።

እመት የሺሐረግ በዳኑ በሦስተኛው ቀን ከሕፃን ልጃቸው ጋር ተኝተው ጡት እያጠቡ በራእይ "ያው ከምንጩ ስጠመቅ የሰማሁት ድምፅ አሁንም ሌሊት መጥቶ እንዲህ አለኝ፣ 'ለምን አትናገሪም? አሁንም ፈተና ይመጣብሻል' እያለኝ ወዲያው ሦስት ጸጉራቸው የተንዠረገገ ጥቋቁር ሰዎች መጡ። ይሄንንም ብሎ እኔንም ልጄንም መታን። ስነቃ መዘዋወር አቃተኝ፤ እኔም ልጄም ታመምን[7]" ይላሉ።

ከምንጩ ሲጠመቁ የሰሙትን መልእክት ለምን እንዳልተናገሩ ምክንያታቸውን ሲገልጹ፤ "ሽማግሌዎች፣ አሮጊቶች፣ ተወልደው ባደጉበት ባረጁበት፣ ከብት የሚጠጣው፣ ሽማ የሚታጠበው እዚሁ! እያልኩ በሓሳብ ተወጥሬ እርሱኑ አስብ ነበር[8]" በማለት የአካባቢው ሰው ይገለገልበት የነበረን የምንጭ ውሃ "ጠበል ነው ብል ማን ያምነኛል" በሚል ሥጋት ሳይናገሩ መቅረታቸውን ገልጸዋል።

[6] ሉቃስ ፲፬፥ ፳፮

[7] እማሆይ ሣህለ ማርያም፣ ዕድሜ ፰፫ (ቃለ-መጠይቅ ሐምሌ ፲፩ ቀን፣ ፳፻፫ ዓ.ም.)።

[8] እማሆይሣህለ ማርያም፣ ዕድሜ ፰፫ (ቃለ-መጠይቅ ሐምሌ ፲፫ ቀን፣ ፳፻፫ ዓ.ም.)።

እመት የሺሐረግ ንገሪ የተባሉትን ባይናገሩም ከምንጩ መጠመቅ ከህመማቸው እንደሚፈውሳቸው በማመናቸው ድጋሚ አላላውስ ካላቸው ሕመም ለመፈወስ በማለዳ ተነሥተው ወደ አስታጥቂ ምንጭ ሄዱ። ደርሰው አስታጥቂ ምንጭ ለመጠመቅ ሲጠጉ ከምንጯ አናት ቀድሞ የሰሙት ድምፅ መጣ። መልእክቱ ቀድሞ የሰሙት አልነበረም። ይህኛው መልእክት ተግሳጽ ሲኾን፣ ይሄውም “አንቺ ሐሰተኛ ተመለሺ ብዬሻለሁ” የሚል ነበር። እመት የሺሐረግም ፈርተው ሳይጠመቁ ተመለሱ። እነዚህን በመሰሉ ፈተናዎች በተደጋጋሚ መፈተናቸው ቀጥሏል።

## ፫.፪ ገዳም እንዲገደም ምክንያት የኾኑ ትርክቶች

በዚህ ክፍል መካነ ሕይወት መድኃኔ ዓለም ደብረ ቁስቋም አንድነት ገዳም እንዲገደም ምክንያት የኾኑ ትርክቶችን እንመለከታለን። እመት የሺ ሐረግ በሕመም ቢሰቃዩም ዳግም ወደ ምንጯ ገብተው ለመጠመቅ አልደፈሩም። ለብዙ ጊዜ ከታመሙ በኋላ በቆጂ ከተማ ወደሚገኘው ወደ ደብረ ፀሐይ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በመሄድ በመቃብር ቤት ሱባኤ በመያዝ፣ በንስሀ አባታቸው ጠበል መጠመቅ ጀመሩ።በዚህም ሳሉ ራእይ ታያቸው። ራእዩም፦

> እንደ ሞተ ሰው በጀርባዬ ተንጋልዬ እንድተኛ ታዘዝኩ። እንደ ተባልኩት በጀርባዬ ተንጋልዬ ተኛሁ። “ልጆቼስ! ልጆቼን!” እንድል ታዘዝኩ። በዚህን ጊዜ እውነተኛውን የሥጋ ሞት በማሰብ ልጆቼ! ልጆቼ! የምላቸው ሳያቸው፣ ሳሳድጋቸው እንጂ ከሞትኩ ወዴት አያቸዋለሁ ብዬ መለስኩ። ይሄንኑ ሦስት ጊዜ ደጋግሜ እንድለው ታዘዝኩ። እንደ ታዘዝኩት ሦስት ጊዜ ደገምኩት። ይሄንንም እንዳልኩ የብዙ ሰዎች ጭብጨባ እና እልልታ ድምፅ ተሰማኝ። ከዚያም፤ ከእንግዲህ ውሃው ጸበል፣ አፈሩ እምነት ነው። ዛፉ መጠለያሽ ነው። ከእንግዲህ ልጆቼ! ከብቶቼ! ትዳሬ! ጎጆዬ! ንብረቴ!...የለም! የለም! የለም! አሁን ከሕመምሽ እንድትድኚ ድርሳነ ሚካኤልን እያስደገምሽ ሦስት ጊዜ ተጠመቂ ትድኛለሽ። ነገር ግን ስትድኚ የምትሄጂው ወደዚያ የምንጭ ውሃ ነው። ወደ ቤትሽ እንዳትገቢ….።[9]

ይሄም የኾነው መጋቢት ፲፱፻፹፮ ዓ.ም. ነበር። ዳግም ልጆቼን ላይሉ ቃል ኪዳን የገቡበት፣ ወደ ፊት ዳግም ወደ ዓለም እንዳይመለሱ የታዘዙበት ራእይ ነበር። ለ፴፫ ዓመታት የኖሩበትን የዓለም ኑሮ የተሰናበቱበት ጽኑ ቃል ኪዳንም ኾነ።

[9] እማሆይሣህለ ማርያም፣ ዕድሜ ፷፫ (ቃለ-መጠይቅ ሐምሌ ፲፩ ቀን/ ፳፻፰ ዓ.ም.)።

እመት የሺሐረግ እንደ ታዘዙት ንስሀ አባታቸው ድርሳነ ሚካኤልን ደግመው እንዲያጠምቋቸው በማድረግ ሦስት ቀን ተጠምቀው ከህመማቸው ሙሉ በሙሉ ዳኑ። ከዳኑ በኋላ በራእይ ወደ ታዘዙበት ሄዱ። ሲሄዱም ለማንም አላማከሩም፤ አልተዘጋጁም፤ እከሌ ናልኝ/ነይልኝ ጫካውን እፈራለሁ፣ አውሬ ይበላኛል! ምንጣፍ አምጡ፣ ይቆረቁረኛል፤ ልጆቼን ልሰናበት፤ ቀለቤን ልያዝ ...ሳይሉ የዘጠኝ ወር ልጃቸው የእናቱን ጡት ሳይጠግብ እንደ ወጡ ቀሩ። የምናኔን ሕይወት ሰው የቆሸሸ ልብሱን በሚያጥብበት፤ ከብት በሚውልበት አራዊት በሚያድርበት ለአዳር ቀርቶ ለውሎ እንኳን በማይመረጠው በአስታጥቄ ምንጭ አጠገብ አደረጉ። ጎንደር ሳሉ ጀምሮ ንገሪ የተባሉትን መናገር ጀመሩ[10]።

፲፱፻፹፯ ዓ.ም. ወቅቱ ዓብይ ፆም ነበር። እመት የሺሐረግ ማልደው ወደ በቆጂ ደብረ ፀሐይ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ሔዱ። እዚያም ደርሰው የጠዋት ጸሎት እንዳበቃ በቤተ ክርስቲያኑ በእለቱ አገልግሎት ላይ ለነበሩት የደብሩ ካህናት ከፈጣሪ የተላኩትን መልእክት ተናገሩ። መልእክቱም፤

> በጨፋ አካባቢ የአስታጥቄ ምንጭ እየተባለ የሚጠራው ስፍራ ከግራኝ አህመድ በፊት የመስቀለ ኢየሱስ፣ ደብረ ቁስቋም እና የአቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ ታቦታት እንደ ነበሩና ቁስቋም የሴቶች፣ መስቀለ ኢየሱስና አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ የወንዶች ገዳም እንደ ነበሩ፤ በወረራው ምክንያት ገዳሙ መውደሙን ገለጹ። ነገር ግን አሁን ጊዜው በመድረሱ ዳግም ቤተ መቅደስ ይሠራል። በስፍራውም ሕሙማነ ሥጋ የሚፈወሱበት ጠበል፣ ሕሙማነ ነፍስ የሚድኑበት ገዳም እንደሚመሠረት ለዚህም በየአጥቢያው ምህላ እንዲያዝ።[11]

በማለት የተነገራቸውን መልእክት ተናግረው ተመለሱ። ግንቦት ፲፪/፲፱፻፹፯ ዓ.ም. ማለዳ እመት የሺሐረግ በድጋሚ ወደ ደብረ ፀሐይ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ሄዱ። ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ በመዝለቅ ካህናቱ የእለቱን ቅዳሴ ጨርሰው ከቤተ መቅደስ እንደ ወጡ እመት የሺሐረግ መልእክቱን እንዲህ ሲሉ ተናገሩ። "ቀኑ ደረሰ! የፈረሰው የእግዚአብሔር ቤት ሊሠራ፤ ለሕሙማን ደኅንነት ይኾን ዘንድ ጸበል የሚፈልቅበት ቀን ዛሬ ነው። ስለዚህ አገልጋይ ካህናት ኑ ወደ ቦታው እንሂድ፤ የእግዚአብሔርን ተአምር ተመልከቱ...።[12]" በማለት ካህናት የሚፈልቀውን ጸበል እንዲባርኩ የሚያሳስብ

---

[10] መልአከ ሕይወት ቆሞስ አባ ኃ/ጊዮርጊስ ይስማ የበቆጂ ጨፋ መካነ ሕይወት መድኃኔ ዓለም ደብረ ቁስቋም አንድነት ገዳም አበምኔት (መስከረም ፲፩ ፳፻፲፪)

[11] በኩረ ትጉሃን በለጠ ኃ/ማርያም የአርሲ ሀገረ ስብከት ጸሐፊና አስተዳደር ክፍል ሓላፊ (ቃለ መጠይቅ፤ መስከረም ፰ ፳፻፲፪)።

[12] በኩረ ትጉሃን በለጠ ኃ/ማርያም የአርሲ ሀገረ ስብከት ጸሐፊና አስተዳደር ክፍል ሓላፊ (ቃለ መጠይቅ፤መስከረም ፳፻፲፪ ዓ.ም)።

መልእክት ተናገሩ። በወቅቱ የደብሩ አስተዳዳሪ[13] የነበሩትና ሌሎችም ወደ ምንጯ እመት የሺ.ሐረግን ተከትለው ሄዱ። በቦታው ሲደርሱ፤ እመት የሺ ሐረግ ከካህናቱ ፊት ለፊት ኾነው በያዙት በትረ መስቀል ከአስታጥቄ ምንጭ በላይ ያለውን መሬት አራት ጊዜ በመውጋት "ይሄ የአቡዬ ጠበል ነው" በማለት አሳዩዋቸው። በዚህን ጊዜ በበትረ መስቀላቸው የወጉበት ቦታ ውሃ ፈለቀ። ከበቆጂ ደብረ ፀሐይ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ-ክርስቲያን አብረዋቸው ከመጡት መካከል አንዱ ካህን[14] ባረኩት። ከዚህ ቀን ጀምሮ ጠበል ኾኖ አገልግሎት መስጠት ጀመረ።

ጠበሉም ለመጠመቅ ምቹ እንዲኾን መሬቱ ከሥር ተቆፍሮ ተስተካከለ። ሕሙማንም በየእለቱ ወደ ጠበሉ በመሄድ ይጠመቁ ጀመር። አፈሩም እምነት ኾኖ መድኃኒት ኾነ። ዛፎች ባይኖሩም የነበሩት ቁጥቋጦዎች እንዲያድጉ ሌላም እንዲተከል ተደረገ። የበቆጂ ደብረ ፀሐይ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ-ክርስቲያን ዲያቆናት ወደ ጠበሉ ስፍራ የሚመጣውን ህዝብ ያጠምቁ ጀመር። ከማጥመቃቸው በፊት መጾም የሚገባቸውን ጾም እና ሌላም ተግባር እንዲፈጽሙ መልእክት በእመት የሺ ሐረግ አማካይነት ተነግሯቸው አጥማቂዎቹ የተባሉትን ፈፀሙ። ከማጥመቁ ጎን ለጎን የጸበሉን ስፍራ በአጥር በመከለል፣ ዛፍ በመትከል እንዲሁም የተለያዩ ሥራዎችን በመሥራት ቦታው ለጸበልተኞች ምቹ እንዲኾን አድርገዋል።

እመት የሺ.ሐረግ በዚሁ ጠበል ስፍራ በየጊዜው የሚነገራቸውን መልእክት መድረስ ላለበት ያደርሳሉ። ሌሊትም በዚሁ በጠበሉ አጠገብ ያድሩ ነበር። ኾኖም በራእይ "ይሄ መዋያሽ እንጂ ማደሪያሽ አይደለም" የሚል መልእክት ደረሳቸው። ትእዛዙን ተቀብለው ከጸበሉ በስተቀኝ ዐምስት መቶ ሜትር ያህል ርቀው የሳር ጎጆ ውስጥ ማደሪያቸውን አደረጉ። ቀን ቀን ከሰው ርቀውና ተሰውረው በጠበሉ ስፍራ ጸሎት በማድረስ ይውላሉ።

እመት የሺ.ሐረግ እንዲመነኩሱ በተደጋጋሚ መልእክት ይነገራቸው ነበር። መልእክቱን በራእይ ከማየት ውጪም የተለያዩ ምልክቶችን ያዩ የነበረ ሲኾን ለምሳሌ ከነገሩን መካከል አንዱ ይህ ነበር። "ነሐሴ መድኃኔ ዓለም ፲፱፻፹፮ ዓ.ም. ከኪሩቤልና ሱራፌል ጸበል አካባቢ ሦስት ሰዓት ሲኾን ደወል ሲደወል ሰማሁ። ደወሉን መቁጠር ጀመርኩ፤ የመጨረሻው ደወል ሲደወል ሰባት ሰዓት ኾነ። ከዚያ በኋላ አልተደወለም። የመጨረሻው ደወል ለሰባተኛ ጊዜ የተደወለ ነበር።" ይህንን ደወል በሰሙ ማግስት ለመመንኮስ ወሰኑ። ስለ መመንኮሳቸው ለእናታቸው ለመንገር ሊሄዱ ሲሉ መሄድ አቃታቸው። ከዚያም ቁጭ ባሉበት እንደ እንቅልፍ አሸልቧቸው የኾነውን ሲገልጹ "ከጠዋቱ አንድ

[13] በወቅቱ የበቆጂ ደብረ ፀሐይ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ-ክርስቲያን አስተዳዳሪ የነበሩት መልአከ ፀሐይ አክሊሉ ነበሩ።

[14] በወቅቱ ጠበሉን የባረኩት ካህን መምሬ ገብረ መስቀል ይባላሉ። ከዚያም በኋላ ፲፱፻፹፰ ዓ.ም. ሚያዚያ ወር በብፁዕ አቡነ ናትናኤል ጋባዥነት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ የቀድሞ የኢ/ኦ/ተ/ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ እና በርካታ ብፁዐን አበው ሊቃነ ጳጳሳት በገዳሙ ተገኝተው ጸበላቱን ባርከዋል።

ሰዓት ገደማ ጀምሮ እስከ ዘጠኝ ሰዓት እጅና እግሬ በሐረግ ታስሮ በጭንቅላቴ ተዘቅዝቄ ዋልኩ[15]::" በማለት የዚህን ቅጣት ምክንያቱን እና ትርጉሙን ሲያብራሩ፣ ለመመንኮስ መወሰናቸውን ለሰው እንዳይናገሩ እና ለማንም ሳያሳውቁ ሌላ ቦታ በመሄድ መንኩሰው እንዲመጡ የተነገራቸው ምልክት መኾኑን ነው:: ለመመንኮስ ማሰባቸውን ለማንም ሳለመናገር ታዝዣለሁ በማለት፣ ለመመንኮስ ተዘጋጅተው የት እንደሚሄዱ ሳይናገሩ ጠበሉን ከሚያጠምቁት ዲያቆናት መካከል አንደኛው[16] ወደ ዝቋላ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ገዳም አብረዋቸው እንዲሄዱ ጠየቁ፤ ሄዱ::

በኢ.ኦ.ተ.ቤ. ሥርዓትና ደንብ መሠረት ጥቅምት ፮/፲፱፻፹፯ ዓ.ም. መነኮሱ:: የዓለም ስማቸው እመት የሺሐረግ የሚለው ቀርቶ፤ እማሆይ ሣህለ ማርያም ተባሉ:: እማሆይ ሣህለ ማርያም ምናኔ በገቡበት ቦታ መኖራቸውን ቀጠሉ[17]::

የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ጠበል ከተባረከ ጀምሮ በበጋ ወራት የጠበል ቦታ ተብሎ በተከለለው በግምት ግማሽ ሄክታር በሚኾነው ቦታ በርካታ ሌሎች የጠበል ምንጮች ፈልቀዋል:: መልእክት ሲነገራቸው የታዘዙበት ቦታ በመሄድ በበትረ መስቀላቸው መሬቱን ይወጋሉ:: ከወጉት መሬት ውስጥ ጠበል ይፈልቃል:: የመነጨው የጠበል ምንጭ በማን ቅዱስ፣ ቅድስት ወይም መልአክ ስም እንደ ተሰየመ በዚያ ላሉት አጥማቂዎች እና ላለው ሰው ይናገሩ ነበር:: ከዚያም በኋላ ምንጮቹ በርካታ በመኾናቸው ያለምንም ምልክት የትኛው የማን ጠበል እንደ ኾነ የሚያውቁት እሳቸው ነበሩ:: ከጠበሉ መፍለቅ በኋላ በአካባቢው ገዳም ተገድሟል፤ ቤተ ክርስቲያን ታንጾ አገልግሎት እንዲሰጥ ተደርጓል::

## ፫.፫ ገዳም የተገደመበትን ስፍራ ቀዳሚ ዳራ የሚያሳዩ ትርክቶች

መካነ ሕይወት መድኃኔ ዓለም ደብረ ቁስቋም አንድነት ገዳም የተገደመበት ቦታ "የአስታጥቄ ምንጭ" ከመመንጨቱ ከበርካታ ዓመታት በፊት ገዳም እንደ ነበረ እማሆይ ሣህለ ማርያም ተናግረዋል:: ከ16ኛው መ/ክ/ዘ በፊት የነበረ ገዳም መኾኑን ይናገሩ እንጂ መቼ የተገደመ እንደ ነበር አልጠቀሙም:: የአንድነት ገዳም የነበረውን "በ፲፮ኛው መ/ክ/ዘ ግራኝ አህመድ ካወደማቸው በርካታ ገዳማት መካከል አንዱ መኾኑን አጽንኦት ሰጥተው ተናግረው ነበር::"[18]

---

[15] እማሆይ ሣህለ ማርያም፣ ዕድሜ ፰፬ (ቃለ-መጠይቅ ኅዳር ፳፫ ቀን/ ፳፻፯ ዓ.ም.)::

[16] በወቅቱ እመት የሺሐረግን ወደ ዝቋላ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ገዳም ይዟቸው የሄደው ዲያቆን በለጠ ኃ/ማርያም ነበሩ:: አሁን በኩረ ትጉሃን በለጠ ኃ/ማርያም የአርሲ ሀገረ ስብከት ጸሐፊና አስተዳደር ክፍል ሓላፊ ናቸው::

[17] መረጃ ሰጭ:- አባ ኪዳነ ወልድ በላይ፣ ዕድሜ ፵፱ ፣የጠበሉ አጥማቂ (ቃለ-መጠይቅ ኅዳር ፳፯ ፳፻፯)::

[18] እማሆይ ሣህለ ማርያም፣ ዕድሜ ፰፬ (ቃለ-መጠይቅ ኅዳር ፳፫ ቀን/ ፳፻፯ ዓ.ም.)::

በሀገራችን ኢትዮጵያ በርካታ ጥንታዊ ገዳማት ያሉ ሲኾን ከእነዚህ ገዳማት መካከል አንዱና ከ፲፮ኛው መ/ክ/ዘ በፊት ለደቡቡ የሀገራችን ክፍል ለገዳማዊ ሕይወት በር ከፋች የነበረ ገዳም እንደ ኾነም ጠቁመዋል፡፡ በወራሪው ኃይል የወደመው የአንድነት ገዳም "የመስቀለ ኢየሱስ እና የአቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ የወንዶች ገዳም" እና "የቊስቋም ማርያም የሴቶች ገዳም" ይባል እንደ ነበረ በትርክታቸው ጠቁመዋል፡፡ ገዳሙ በግራኝ አህመድ እስኪወድም ድረስ በገዳሙ ውስጥ አባቶች እና እናቶች በገዳም ሥርዓት መሠረት ገዳማዊ ሕይወታቸውን ይመሩ እንደ ነበረ ባህታዊት እናት እማሆይ ሣህለ ማርያም ተናግረዋል፡፡

በ፲፮ኛው መ/ክ/ዘ በመላው የሀገራችን ክፍሎች የግራኝ አህመድ ጦር በርካታ አብያተ ክርስቲያናትን በማውደም ካህናትን በሰየፉበት ወቅት የእነዚህ ሁለት ቤተ መቅደሶችና ገዳም ዕጣ ፋንታ በወራሪዎች መቃጠልና መውደም ነበር፡፡ ኾኖም ሁለቱም እንዲቃጠሉ ቢሞከርም የተቃጠለው የመስቀለ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን እንደ ኾነ ተናግረዋል፡፡ የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቤተ-ክርስቲያን እንደ ነበረ ጠቊመው እርሱም በጦርነቱ ወቅት በራሱ ጊዜ መሰወሩን ጠቊመውናል፡፡ በወቅቱ በገዳሙ ያሉ መነኮሳት አባቶች በከፊል ንዋያተ ቅድሳቱን ይዘው መሸሻቸውን፤ እኩሌቶቹም በዚያው በገዳሙ የሰማዕትነት ጽዋ መቀበላቸውን እማሆይ ሣህለ ማርያም በትርክቱ ገልጸዋል፡፡

በተለያየ ጊዜም ይሄንኑ የሚያሳዩ የተለያዩ ንዋያተ ቅድሳት፣ የመቃብር ምልክቶች የሰው አጽሞች ተገኝተዋል፡፡ ይህ የሰዎች አጽም በግራኝ አህመድ የተገደሉ ገዳም ውስጥ የነበሩ መነኵሳትና የገዳሙ አገልጋዮች እንደ ኾኑ እማሆይ ሣህለ ማርያም ተናግረዋል[19]፡፡

በግራኝ አህመድ ጠፍቶ የነበረው የአንድነት ገዳም፤ በዚህ ዘመን በእኚህ እናት መልእክተኝነት ተመልሶ ተገድሟል፡፡ በዚህ መሠረት በዚህ ስፍራ በእማሆይ ሣህለ ማርያም አሳሳቢነት ይሄንን ገዳም ቀድሞ ወደ ነበረበት ይዘቱ እንዲመለስ በራእይ የሚነገራቸውን በመናገር እንዲሠራ በፆም በጸሎት ከፍተኛ ተጋድሎ በማድረግ በርካታ መንፈሳዊ አገልግሎት የሚሰጥባቸው ሥራዎች ተሠርተዋል፡፡ በራእይ ከተገለጠላቸው መካከል በቦታው ላይ ይኾናል የሚሉት ኾኖም "ጊዜው አልደረሰም" የሚሉትንም ጊዜው ሲደርስ እንደሚገለጥ በመናገር፣ ምልክት የሚደረግባቸውን በማድረግ የትጋ ምን እንዳለ መቼ እንደሚገለጥም ጭምር ይጠቁሙ ነበር፡፡ ቀድሞ በግራኝ አህመድ የወደመ ገዳም ነበር ያሉት የአሁኑ "መካነ ሕይወት መድኃኔ ዓለም ደብረ ቊስቋም አንድነት ገዳም" ጨምሮ በቦታው እስከ አሁን መሠራት ከነበረባቸው መካከል እማሆይ ሣህለ

[19] መረጃ ሰጭ፡- አባ ኪዳነ ወልድ በላይ፣ ዕድሜ ፺፱፣ የጠበሉ አጥማቂ (ቃለ-መጠይቅ ኅዳር ፳፯ ፳፻፯ዓ.ም.)፡፡

ማርያም የተናገሯቸውን ትርክቶች መሠረት አድርገው የተሠሩት የሚከተሉት ናቸው።

## ፫.፬ ትርክቶቹን ተከትሎ በተግባር የተከናወኑ ተግባራት

ትርክቶቹን መነሻ በማድረግ ከተሠሩት ሥራዎች መካከል የመካነ ሕይወት መድኃኔ ዓለም ደብረ ቁስቋም አንድነት ገዳም መገደም ዋንኛው ተግባር ነው። ይህ ተግባር ዓመታትን የፈጀ ሂደት ነበረው። ገዳሙ የተገደመበትን ቦታ ከግለሰቦች በስጦታም በግዢም ወደ ቤተ ክርስቲያኗ ይዞታ ማካተት ቀዳሚው ተግባር ሆኗል። አርባ ሁለት የጠበል ምንጮች ፈልቀው አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ። ሁለት ሕንጻ ቤተ ክርስቲያናት ተገንብተው አገልግሎት በመስጠት ላይ ናቸው። በገዳም ውስጥ በርካታ መነኮሳት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ደንብ ይተዳደራሉ[20]። እነዚህም መቼ እና እንዴት እንደ ተደራጁ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

በቀዳሚነት ጠበሉ ግንቦት ፲፪ ቀን ፲፱፻፹፮ ዓ.ም. ተባረከ። የበቆጂ ደ/ፀ/ቅ/ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ የነበሩት ካህን[21] የእማሆይ ሣህለ ማርያምን መልእክት በመቀበል በወቅቱ የደብሩ አገልጋይ የነበሩትን ካህን ወደ ስፍራው በመላክ ጠበሉን አስባርከዋል። ይህ ታሪክም ለብፁዕ አቡነ ናትናኤል የቀድሞ የአርሲ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስና የቅዱስ ሲኖዶስ አባል እንዲያውቁት ተደረገ። ይህንንም ያሳወቁት በወቅቱ የሌሙና ቢልቢሎ ወረዳ ቤተ ክህነት ሓላፊ የነበሩት[22] ግለሰብ ናቸው። እማሆይ ሣህለ ማርያምም በአካል አቡነ ናትናኤል ዘንድ ቀርበው "ከፈጣሪ ተነገረኝ" ያሉትን ብፁዕነታቸውም ሊያደርጉ የሚገባቸውን ጭምር በዝርዝር ተናገሩ[23]። ብፁዕ አቡነ ናትናኤል ወደ ስፍራው በመሄድ የተባለውን ተመለከቱ። በጸበሉም ሕሙማን ሲጠመቁና ሲድኑ በመመልከታቸው "የእግዚአብሔር ፈቃድ ይኹን" በማለት የእግዚአብሔርን ሥራ በማድነቅና ቀደም ሲል በእማሆይ ሣህለ ማርያም የተነገራቸውን በዓይናቸው ስለ ተመለከቱ ጠበሉ በብፁዕነታቸው ተባረከ። በስፍራውም ለምዕመናን አገልግሎት የሚሰጥ ቤተ ክርስቲያን በአስቸኳይ እንዲሠራ መመሪያ ሰጡ።

በወቅቱ የገዳሙ መሥራች የነበሩት እማሆይ ሣህለ ማርያም በፈቃደ እግዚአብሔር ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን የሚሠራበት ቦታ ቀደም ሲል ከግራኝ አህመድ ወረራ በፊት ታቦተ መስቀለ ኢየሱስና ታቦተ ገብረ መንፈስ ቅዱስ የነበሩበት እንዲሁም "በርካታ ካህናት ተሰውተውበታል" ያሉበትን ቦታ በማመልከት እዚያው ቦታ ላይ ቤተ ክርስቲያኑ

---

[20] መልአከ ሕይወት ቆሞስ አባ ኃ/ጊዮርጊስ ይስማ የበቆጂ ጨፋ መካነ ሕይወት መድኃኔ ዓለም ደብረ ቁስቋም አንድነት ገዳም አበ ምኔት (ቃለ መጠይቅ፣ ጥቅምት ፳፮/ ቀን ፳፻፲፪ ዓ.ም.)

[21] በወቅቱ የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ የነበሩት መልአከ ፀሐይ አክሊሉ ገ/ኪዳን ናቸው።

[22] በወቅቱ የወረዳ ቤተክህነቱ ሃላፊ የነበሩት ሊቀካህናትተክለጻዲቅ ነበሩ።

[23] ብፁዕ አቡነ ናትናኤል የቀድሞ የአርሲ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ (ቃለ መጠይቅ ሐምሌ ፳፯ ቀን ፳፻፯)።

እንዲሠራ ብለው ነበር፡፡ ኾኖም በተለያዩ ምክንያቶች የግንባታው ሥራ በግምት እማሆይ ሣህለ ማርያም ካሉበት ሦስት መቶ ሜትር ያህል ርቆ ተሠርቶ ጥቅምት ፳፯/፲፱፻፹፯ዓ.ም. ቅዳሴ ቤቱ ተከብሮ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡

እማሆይ ሣህለ ማርያምም የመድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን መቅደሱ ይሠራበት ባሉበት ቦታ ላይ ከ፲፱፻፹፯ ዓ.ም. ጀምሮ ከለላ ሠርተው ጠዋት የኪዳን ጸሎት፣ ቀን በስድስት ሰአት ጸሎት ማድረሻ፣ ቅዳሴ ማስቀደሻ ቋሚ ስፍራ አደረጉት፡፡ ስፍራውን የመረጡበት ምክንያት በቦታው ብዙ ቅዱሳን አጽማቸው አርፎበታል የሚል ራእይ ስለ ተገለጠላቸው ነበር፡፡ ስለዚህ "የመድኃኔ ዓለም ቤተ-ክርስቲያን ቀድሞ ግራኝ አህመድ አቃጠለው በተባለው መስቀለ-ኢየሱስ ቤተ-ክርስቲያን እና መሰወሩ በታመነበት አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቤተ-ክርስቲያን ምትክ የመድኃኔ ዓለም ቤተ-ክርስቲያን እንዲሠራ" ተነግሮኛል ባሉት መሠረት አዲሱ የመድኃኔ ዓለም ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን እንዲሠራ በሀገረ ስብከቱ ተወሰነ፡፡

በ፳፻፫ ዓ.ም. በብፁዕ አቡነ ናትናኤል የቀድሞ የአርሲ በሀገረ ስብከት ሊቀጳጳስና የቅዱስ ሲኖዶስ አባል የመሠረት ድንጋይ ተጣለ፡፡ እማሆይ ሣህለ ማርያምም የጸሎት ቦታቸውን ቀየሩ፡፡ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያኑን ለመሥራት መሬቱ ሲቆፈር እማሆይ ይናገሩ እንደ ነበረው የበርካታ ቅዱሳን አጽም ተገኘ፡፡ የተገኙት አጽሞች በዚያው በመድኃኔ ዓለም ግቢ በክብር እንዲያርፉ ተደርጓል፡፡ አዲሱ የመድኃኔ ዓለም ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን የግንባታ ሥራው ተጠናቋል[24]፡፡

የመድኃኔ ዓለምን ቤተ-ክርስቲያን ጨምሮ "የጨፋ መድኃኔ ዓለም፣ ደብረ ቁስቋም ቅድስት ማርያምና ቅድስት ሰሎሜ የሴቶች አንድነት ገዳም" ተብሎ መጋቢት ፲፱፻፹፰ ዓ.ም. የአርሲ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስና የቅዱስ ሲኖዶስ አባል በነበሩት በብፁዕ አቡነ ናትናኤል ተሰየመ፡፡

እማሆይ ሣህለ ማርያም ከግራኝ ጥፋት በፊት እንደ ነበረው፤ የወንዶችም የሴቶችም የአንድነት ገዳም እንዲኾን በጠየቁት መሠረት በ፳፻፪ ዓ.ም. እንደ ገና ተሻሽሏል፡፡ ይኸውም የሴቶች ገዳም ብቻ መኾኑ ቀርቶ "የጨፋ መድኃኔ ዓለም ደብረ ቁስቋም፣ ቅድስት ማርያም ወሰሎሜ አንድነት ገዳም" ኾኖ አሁንም በዚሁ መጠሪያና ደንብ ይተዳደራል፡፡

[24] ሙሉ በሙሉ የሕንጻ ቤተ ክርስቲያኑ ሥራ ተጠናቅቆ ሚያዝያ ፳፯ ቀን ፳፻፲፪ ዓ.ም. ሊመረቅ በዝግጅት ላይ ነበርን፡፡ ኾኖም በዓለም ብሎም በሀገራችን በተከሠተው ወረርሽኝ (COVID 19) ምክንያት የሕንጻ ቤተ ክርስቲያኑን ምረቃ ላልተወሰነ ጊዜ አራዝመነዋል፡፡ (መልአከ ሕይወት ቆሞስ አባ ኃ/ጊዮርጊስ ይስማ፤ የበቆጂ ጨፋ መካነ ሕይወት መድኃኔ ዓለም ደብረ ቁስቋም አንድነት ገዳም አበ ምኔት፤ በስልክ የተደረገ ቃለ መጠይቅ፣ ግንቦት ፪ ቀን ፳፻፲፪ ዓ.ም.)፡፡

እንደ መድኃኔ ዓለም ቤተ-ክርስቲያን ሁሉ በግራኝ አህመድ እስኪወድም ድረስ በሴቶች ገዳም የቁስቋም ቤተ ክርስቲያን እንደ ነበረ እና የነበረበትን ቦታ ጭምር እማሆይ ሣህለ ማርያም አመልክተዋል። እንዲሁም ቀደም ሲል ወድሟል ባሉበት ቦታ ላይ በምትኩ መሠራት ያለበት የኪዳነ ምህረት ቤተ ክርስቲያን እንደ ኾነ ተናግረው ነበር። እማሆይ ሣህለ ማርያም በተናገሩት ትርክት መሠረት የኪዳነ ምሕረት ሳይኾን የቁስቋም ቤተ-ክርስቲያን ተሠርቷል። ይህም የቁስቋም ቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ተሠርቶ ከኀዳር ፮ ቀን ፳፻፪ ዓ.ም. ጀምሮ ንዋያተ ቅድሳቱ ተሟልቶለት አገልግሎት እየተሰጠበት ይገኛል።

የበቆጂ ጨፋ መካነ ሕይወት መድኃኔ ዓለም ደብረ ቁስቋም አንድነት ገዳም አሁን ባለበት ደረጃ ዐሥራ ሰባት ሴት መነኲሳት እና ዐሥራ ዐምስት ወንድ በድምሩ ሠላሳ ሁለት መነኲሳት ይኖሩበታል። ገዳሙ በራሱ ገቢ የሚተዳደር ሲኾን ለዚህም ገዳማውያኑ የተለያዩ ሥራዎችን ያከናውናሉ። ከሚሠሯቸው ሥራዎች መካከል የእደ ጥበብ ምርቶች፣ እርሻ፣ ከብት እርባታ እንዲሁም አንድ የእህል ወፍጮ በማቋቋም ራስ አገዝ በኾነ መንገድ ገዳሙ ይተዳደራል። ሥራውን የሚሠሩት በገዳሙ ውስጥ ያሉ መነኲሳት ሲኾኑ አንዳንዴ በጎ አድራጊዎችም በገንዘብም ኾነ በተለያዩ መንገዶች እገዛ ያደርጉላቸዋል።

ይህ ገዳም በዚህ መልኩ እንዲደራጅና አሁን ከሥጋ ሕመም ለመፈወስ የሚመጡ ሕሙማን የሚፈወሱበትን የጠበል ስፍራ እዚህ እንዲደርስ በየጊዜው ለሚመለከተው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አካል በማመልከት፣ በምንኩስናና በብኅትውና ጭምር በዚያው በጠበሉ ስፍራ ባለ ጫካ ውስጥ በመኖር ትርክቶቹን ከጅምሩ እስከ ፍጻሜው የተናገሩት እማሆይ ሣህለ ማርያም ነበሩ።

ከዚህ በላይ የቀረቡትን ትርክቶች እንዲሁም በከፊል ታሪካቸውን የነገሩን እማሆይ ሣህለ ማርያም ሲኾኑ ጊዜውም ከ፳፻፬ እስከ ግንቦት ፩ ቀን ፳፻፯ ዓ.ም. ድረስ ያለውን ያጠቃልላል። እማሆይ ሣህለ ማርያም ሰኔ ፲፯ ቀን ፳፻፯ ዓ.ም. በ፹፬ ዓመታቸው ከዚህ ዓለም ድካም አርፈዋል። ለ፳፩ ዓመት በጸሎትና በብኅትውና ተወስነው በኖሩበትና በገዳሙ ውስጥ ባለው የጸሎት ቤታቸው ዐጽማቸው በክብር አርፏል።

እናታችን እማሆይ ሣህለ ማርያም በእግዚአብሔር ፈቃድ ለዚህ አገልግሎት ከተጠሩበት ቀን አንሥቶ በአምላካችን ፊት ታዛዥ፣ ከክፋት የራቁና እውነተኛ የሃይማኖት ሰው ነበሩ። እግዚአብሔር በሰጣቸው ጸጋ በጸሎት ሲተጉ እና መልካሙን የእምነት ገድል ሲጋደሉ የቆዩ ሲኾን እሳቸው ጥለውት ያለፉት በጎ ሥራቸው ለዚህ ትውልድ ታላቅ አርአያ ነው።

ሲሉ በወቅቱ የገዳሙ መሥራችና የበላይ ጠባቂ  የነበሩት ብፁዕ አቡነ ናትናኤል የአርሲ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስና የቅዱስ ሲኖዶስ አባል ተናግረው ነበር[25]።

## ፬. ማጠቃለያ

ይህ ጽሑፍ መካነ ሕይወት መድኃኔ ዓለምና ደብረ ቁስቋም አንድነት ገዳምን የሚመለከቱ በተለይም ለመገደሙ ምክንያት የኾኑ ትርክቶችን ያሳየ ጥናት ነው። የትርክቶቹም መነሻ ራእይ ነው። እማሆይ ሣህለ ማርያም በተለያዩ ጊዜያት ያዩትን ራእይ ይመለከተዋል ለሚሉት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታይ ምእመን እንዲሁም የተለያየ ሥልጣን ላላቸው አካላት ያሳውቁ ነበር። ትርክቶቹንም አንዱ ለሌላው እየነገረና እየተረጎመ በተግባር በሚገለጥና በሚዳሰስ መልኩ ተግባር ላይ ውለዋል።

ትርክቱ አሁን ገዳም የኾነው ቦታ ሳይታወቅ የኖረ ታሪክ እንዳለውም የሚጠቁም ነው።ይሄውም ከ፲፮ኛው መ/ክ/ዘ በፊት የወንዶች እና የሴቶች አንድነት ገዳም እንደ ነበረ መናገሩ ነው። ገዳሙ በ፲፮ኛው መ/ክ/ዘ በግራኝ አህመድ ወረራ ምክንያት እንደ ተቃጠለ ከፊሉም እንደ ተሰወረ እና በገዳሙ ይኖሩ ከነበሩ መነኰሳት እና አገልጋዮች ውስጥ ጥቂቶቹ ንዋያተ ቅድሳትን ይዘው የሸሹ ሲኾን ሌሎቹ ደግሞ ከገዳሙ መቃጠል ጋር መስዋእት በመኾን አጽማቸው በዚሁ ቦታ ላይ እንዳረፈ ከትርክቶቹ ያገኘናቸው መረጃዎች ያመለክታሉ።

ትርክቶቹን በተግባር እንዲገለጡ ያደረጋቸው ለራእዩ ሃይማኖታዊ ፍቺ መስጠቱ ነው። እማሆይ ሣህለ ማርያም ራእያቸውን መነሻ በማድረግ ትርክቶቹ በተግባር እንዲለወጡ ማሳሰብ ብቻ ሳይኾን በግለሰብ ደረጃ አኗኗራቸው ጭምር ተለውጦ በገዳሙ በምናኔ እና በምንኩስና ለሃያ አንድ ዓመታት ኖረዋል። እኚሁ እናት ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው ትርክቶችን በመናገር ከዚህ ዓለም እስከ ተለዩበት እስከ ሰኔ 16 ቀን ፳፻፮ ዓ.ም. ድረስ በተግባር ለኾነው ብቻ ሳይኾን “ወደ ፊት ይገለጣል፤ ጊዜው ገና ነው” ያሏቸውንና ያዩትን ትርክቶችም ተናግረዋል።

በትርክቶቹ መሠረት ሌላ ተጨማሪ ምስክር ሳያስፈልግ ገዳም ተገድሟል። የትርክቶቹ ይዘት፤ ቀድሞ የአንድነት ገዳሙ ከየት እስከ የት እንደ ነበር፣ የት ቦታ ላይ ምን እንደ ነበረ እና መልሶ መሠራት ያለበት የት እና እንዴት መኾን እንደሚገባውም አመላክቷል። እነዚህን ትርክቶች ተከትሎም ከቀድሞው የአርሲ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ናትናኤል ጀምሮ ከሌሎች አገልጋዮች ጋር በመኾን በርካታ ሥራዎች

[25] ቃለ መጠይቅ (ሐምሌ ፳፭ ቀን ፳፻፮ ዓ.ም.)።

ተሠርተዋል። ትርክቶቹን ተከትለው ከተሠሩት ሥራዎች መካከል፤ ከግንቦት ፲፱ ቀን ፲፱፻፹፮ ዓ.ም. የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ጠበል ከፈለቀበት ጀምሮ ከአርባ ሁለት በላይ የጠበል ምንጮች ፈልቀው ተገቢው ሥራ ተሠርቶ ለሕሙማን አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ። ከጥቅምት ፳፯ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ.ም. ጀምሮ የመድኃኔ ዓለም ቤተ-ክርስቲያን እንዲሁም የቁስቋም ቤተ-ክርስቲያን ከኅዳር ፯ ቀን ፳፻፫ ዓ.ም. ጀምሮ አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ። በ፳፻፱ ዓ.ም. የሴቶች አንድነት ገዳም፣ በ፳፻፫ እንደገና የሴቶችና የወንዶች አንድነት ገዳም ኾኖ በመሻሻል ገዳም ተገድሞ ከ፵፱ በላይ መነኰሳት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት መሠረት በአንድነት ገዳም ደንብ መሠረት አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል።

## ዋቢ መጻሕፍት


ሉሌ መላኩ:: (፲፱፻፹፯):: *የቤተ ክርስቲያን ታሪክ::* ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት::

ምክረሥላሴ ገብረማርያም:: (፳፻):: *የእግዚአብሔር መንግሥት ታሪክ በምድር ላይ* (ጠቅላላ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ፪ተኛ መጽሐፍ):: አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት::

ሞገስ ጀንበሩ:: (፳፻፫):: *ከዳጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም አመሠራረት ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮች እና አምልኳዊ ሥርዓቶች::* [ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ]:: ዐዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ::

ሰለሞን ዮሐንስ:: (፳፻፩):: *የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ወርቃማ ዘመን::* ባናዊ ማተሚያ ቤት::

ስሜ ታደሰ:: (፳፻፩):: *የቤተ ክርስቲያን ታሪክ*:: ኤስ አይ ኤም ፕሬስ::

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ:: (፲፱፻፵፰):: *መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ መዝገበ ቃላት ሀዲስ*:: አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት::

ገሰሰ ፋሪስ:: (፲፱፻፺፰):: *ሐመረ ክርስትና በመዋግደ ፍልስፍና*:: ሜጋ ማተሚያ ቤት::

ወርቁ ከተማ:: (፳፻):: *የሌሙና ቢልቢሎ ወረዳ፣ የጨፋ መድኃኒዓለም፣ ደብረ ቁስቋም፣ ቅድስት ማርያምና ቅድስት ሰሎሜ የሴቶች አንድነት ገዳም፣ መሠራረት ፎክሎራዊ ገጽታ::* [ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ]:: ዐዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ::

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች አካዴሚ:: (፳፻፪):: *የአማርኛ መዝገበ ቃላት::* ዐዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ፕሬስ ::

*ያረጋል አበጋዝ*:: (፲፱፻፺፫):: *ፍኖተ ቅዱሳን*:: (*ማተሚያ ቤቱ ያልታወቀ*)::

*ዳንኤል ክብረት*:: (፳፻፲፩):: *ኢትዮጵያዊው ሱራፌ፤ የአቡነ ተክለ ሃይማኖት የሕይወት ታሪክና አስተዋጽዖ*። ፋርኢስት ትሬዲንግ ኃላ.የተ.የግ.ማኅበር::

ፍሬሕይወት ባዩ:: (፳፻፲፪ እ.አ.አ.):: የጠበል ፎክሎራዊ ገጽታ በጨፋ/በጎንዴ ጠበል ማሳያነት:: *ዜና ልሳን:: የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች አካዳሚ መጽሔት.* ፳፯(፩)፣ገጽ ፩-፲፱::

Kothari, C.R.(2004).Research methodology. New Age International Publishers.

Tsirpanlis, N.C. (1991). Introduction to Eastern patristic thought and Orthodox theology. Liturgical Press